ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band


*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ህዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

## የሾላ ዛፍ ማፍራት የጠቀመው ለአዕዋፍ ነው

## ዛፉ አልተጠቀመም !

በኢትዮጵያ ሕዝብ የረዥም ዘመናት ታሪክ ሂደት፤ ገናና የታሪክ ምዕራፍ አስመዝግቦ አልፏል የተባለለት፤ የየካቲት ወር 1966 ዓመት ምህረት ዐብዮት ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐብዮት ! ኢትዮጵያዊ ዐብዮት ነበረ ! ያልተዳቀለ፤ ያልተበረዘ፤ ያልተዘነቀ፤ ያልተበወዘ፤ ያልተለወሰ ያልተደረተ፤ ወጥ ( ኦርጂናል ) የሆነ ኢትዮጵያዊ ዐብዮት ነበር። የኢትዮጵያም ሕዝብ አንጡራ ዐብዮት ነበር ። እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከውጭ ያልገባ ! ከኢትዮጵያ ሕዝብ አመፅ ተርግዞ፤ ከኢትዮጵያ ማህፀን የተወለደ ኢትዮጵያዊ ዐብዮት ነበር ። በዜግነቱ፤ በትውልዱ፤ በባህሪውና በጠባዩ፤ በዓላማውና በራዕዩ ኢትዮጵያዊ ዐብዮት ነበር ! መነሻው፤ መገስገሻውና መዳረሻው፤ ዓላማውና ግቡ፤ ምኞቱና ተስፋው፤ ሀገሪቱ፤ ከነበርች ኋላ-ቀር አገዛዝ፤ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተሸጋግራ፤ በልጽጋ፤ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ነበር ። ነፃነቷንና ባኅሏን፤ ታሪኳንና ዕምነቷን ፤ አስከብራ፤ ጉራማይሌ መልክ ያላቸው ዜጎቿ በዕኩልነት እየኖሩ፤ አንድነታቸውንና ዕምነታቸውን ፤ ጠብቀው ወደ ተራማጅ ኅብረት ሰብ ተሸጋግረው ፤ በነፃነት እንዲኖሩ ነበር ። ከብዝበዛ፤ ከምዝበራና ከጭቆና የጸዳ ሥርዓት ማግኘት፤ የመላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ምኞትና ተስፋ ነበረ። ለዚህም አይከፍሉ መሥዋዕት ተከፍሎበታል ። በኢትዮጵያን ሕዝብ መሥዋዕት የተገኘን ድል ግን ሌሎቹ ተጠቀሙበት ። የሾላ ፍሬ የጠቀመው ለዛፉ ሳይሆን ለአዕዋፋቱ እንደሆነው ሁሉ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዐብዮትም ገንጣዮችና አስገንጣዮች ተጠቀሙበት ። " **ከሞኝ ደጃፍ፤ ብልኅ ሞፈር ይቆርጣል !** " እንዲሉ !

ሀገራችን በዘመናት፤ ወራሪ ቅኝ ገዥዎችን፤ የባዕዳንን ጣልቃ-ገብነት ሁሉ ተዋግታ ነጻነቷን ጠብቃ ቆይታለች ። የምሥራቁንም ሆነ የምዕራቡን ተጽእኖ ተከላክላ፤ ሀገራዊ ክብሯን አስከብራ ኖራለች ። በዘመነ ቅኝ አገዛዝ/ኮሎኒያሊዝምና ኢምፔርያሊዝም ነጻነቷን ጠብቃ የቆየች ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር በመሆኗ የጥቁር ሕዝብ ሁሉ የነጻነት ተምሳሌት ነበረች ። ይህም ፤ ከበሬታና አድናቆትን አትርፍሮላታል ። የዛሬውን አያድርገውና !

የነበር ሲወጋ ይመስላል ያልነበር፤ ታሪክ ተደፋፍኖ ተሸፋፍኖ ሊኖር ?

የመቅደላው ወኔ ፤ የመተማው አፅም ፤ የአደዋው ጀግነነት እንዲህ ሆኖ ሊቀር ?

የታጋዮቿ መሥዋዕት ፤ የሕዝቦቿ ተስፋ ያገራችን ራዕይ፤ የዐብዮቱ ዓላማ ፤

ሲያስተጋባ ኖሮ፤ የሕዝባችንን ምሬት፤ የትውልዱን ምኞት በገጠር - ከተማ፤

መች እንዲህ ይቀራል ድል ሳይጎናጸፍ በሕዝቡ አደባባይ ፤ በኢትዮጵያ ማማ ።

ልብ ያጣ ልብ ይግዛ ፤ ልብ ያለው ልብ ይበል፤ ይቅር አንገት መድፋት ፤

ይቅር መጠፋፋት ፤ በሆነ ባልሆነው፤ አንዱን ሌላው መጥለፍ ፤ ዕርስ በዕርስ መራኮት፤

ዒላማህን ዕወቅ፤ ዓላማህን አንግብ፤ ጠላትህን ለይተህ ፤ ከወገን ተዘነቅ ፤

ተባብረህ ተገናኝ ፤ ተስማምተህ ተወያይ፤ ዓላማህን አውቀኽ ፤ ዝናርህን ታጠቅ

መሥዋዕት ለመክፈል፤ ቆርጦ ለመታገል ፤ ተበብረህ ተነሳ፤ ቀብቶህን ኣጥብቅ ፤

ሰላዮችን መንጥር፤ ወሬዮችን አባር፤ ባዕዳን አስዋግድ፤ ከጠላት ተጠንቀቅ ።

ይህንን አድርገህ፤ ቁም -ነገር ካልሰራህ፤ አገርክን ካላዳንክ፤ ድል ካልተጎናፀክ ፤

ታሪክ አስመዝግበህ፤ ፤ እንደ አያት- ቅድመ- አያት፤ ትውልድ ካላኮራህ ፤ ነፃ ካላወጣህ፤

ሀገርክን ሳታድን፤ ሕዝብን ሳትታደግ፤ ተዋርደህ እየኖርክ፤ ሞተህ ትሞታለህ ።

ሀገሪቱ ጠፍታ ፤ አንተም ትጠፋለህ፤ ዘር ማንዘርህ ጠፍቶ፤ በንነህ ትቀራለህ !

**" ተባብረህ ተስማምተህ ከአልረገጥክ ዕርካብ "**

**ዓላማህ ይሆናል የዕምቧይ ካብ የዕምቧይ ካብ "**

ብሎ አስጠንቅቆሃል፤ ጽፎ አስነብቦሃል፤ ተንብዮ ነግሮሃል፤

ያ ድንቅ ዳራሲ፤ ኢትዮጵያዊው ምሁር፤ ከበደ ሚካኤል ።

የየካቲት ሕዝባዊ ዐብዮት ከፈነዳ ዐርባ፤ ዓመቱን አስቆጠረ ። የሕዝቡን አመፅ በመንጠቅ ለባዕዳን ያሰረከቡት ቡድኖችም፤ ሀገሪቱን እዚህ አሁን ከደረሰችበት አዘቅት እንድ ትወድቅ ምክንያት ከሆኑ በኋላ፤ እነርሱም እራሳቸው፤ በአሳፋሪ ሁኔታ አጥፊና ጠፊ ሆነው ጠፍተዋል ። ሀገሪቱ ግን ጠላቶቿ እንደ ሚመኙላት ጠፍታ አልጠፋችም ። ቢሆንም፤ ከህያው በታች ከሙታን በላይ ሆና ግን ትገኛለች ። ይህንን ወቃታዊ ሁኔታ ያልተገነዘበ ዜጋ አለ ለማለት ያስቸግራል ። ከዐርባ ዓመታት በኋላ፤ ኢትዮጵያ

የት ደርሳለች ? የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ግን፤ ራስን ከስሜታዊነትና ከቂም በቀል ነጻ አድርጎ ማየትና መገምገም ያስፈልጋል ። ይህንን ለማለት የምንገደደው በሦስት ዐበይት ምክንያቶች ነው።

1ኛ. በሰከነና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ፤ የወደፊቱን የትግል ሂደትና ግብን፤ስትራተጂ ለመቀየስ !

2ኛ. ሚዛናዊና ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ሁኔታዎችን ለመገምገም ፤

3ኛ. የካቲት ዐብዮት ያስመዘገበውን ፋይዳና ትርፍ በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ያስከተለውን ኪሳራ ለማየት እንዲቻል ነው ።

እነኝህን ነጥቦች ያካተተ ትንታኔና ግምገማ ማድረግ ከተቻለ፤ ሁሉ-አቀፍ ከሆነ ድምዳሜ መድረስ ይቻላል ተብሎ ይታሰባል ። "ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራለትም። " የሚለው ይትብሃል፤ ያለፈው እንዲረሳ የሚጋብዝ አባባል መስሎ ቢታይም፤ ታሪኩን በተገቢው ግንዛቤ አስቀምጦ ግን፤ በወደፊቱ የሀገራችን መፃዒ ዕድል ላይ ብቻ ማተኮሩ ይመረጣል ብለን አናስባለን ። ያለፈውን መከራና ደስታ በታሪክ ማህደር እንዲቀመጥ በማድረግ፤ ስለ ወደፊቱ የሀገራችን ኢኮኖሚ ዕድገት፤ የዴሞክራሲያ ሥርዓት፤ ሠላምና ደኅንነት ፤ ነፃነትና የሀገር ግዛታዊ አንድነት ተግቶ መስራቱ ይመረጣል ። ይህ ደግሞ በራሱ ፈቃድና ምኞት ብቻ የሚመጣ አይሆንም ። ተግቶ መስራትንና ወደ ተፈለገው ግብ ሊያደርስ የሚያስችለውን ስልትና ዘዴ ( ስትራተጂ ) መቀየስን ይጠይቃል ። ለዚህ ተግባር ደግሞ፤ በግድ፤ የሁሉንም ኅብረተ- ሱታፌ ይፈልጋል ። አግላይ ፖለቲካ ምኅዳር፤ እንደ ኢትዮጵያ ላለ ኅብረ- ብሄር አገር አይሰራም። ለዚህም፤ በወያኔ ኅጠኛ አገዛዝ ተጨባጭ ማስረጃ ሆኗል ። ያለ ኅብረ-ፓርቲ ሙሉ ተሳትፎ ፤ ሠላምና መረጋጋት ሊመጣ አይችልም ። ይመጣል ከተባለ፤ የዴሞክራሲን ደብዛ ኣጥፍቶ፤ በአንድ ፈላጭ-ቆራጭ አምባገነን ፓርቲ በሚገዛ ሥርዓት ብቻ ነው። ያም ቢሆን ዘላቂ ሠላምን ሊያመጣ አይችልም ። ይህ ሁኔታ ባለፉት አርባ ዓመታት የተፈራቁት አምባገነኖች የፈፀሙት ወንጀል፤ ሀገሪቱ የት ደርስለች ? ለሚለው ዐብይ ጥያቄ መልስ ይሰጣል ።

እስካሁን ድረስ መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎች መልስ አላገኙም፡-- እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ. መሬት ላራሹ የተበለው ጥያቄ፤ ለኣራሹ ሳይሆን፤ በመንግሥት ዕጅ / ቁጥጥር ስር ሆኗል ።

ለ. ዴሞክራሲ፤ ፍርድ- ፍትኅ- ርትዕ ደብዛቸው ጠፍቷል።

ሐ. የሕዝቡ ኑሮ ደረጃ እያደር ቁልቁል እየወረደ ይገኛል ። ባንፃሩ ግን የኑሮ ውድነት ሰማይ-ጠቀስ ሆኗል ። ለሰፊው ሕዝብ የሚሆን የምግብ አቅርቦት ዋጋ ከቁጥጥር በላይ ስለሆነ፤ የአንድ ዶሮ ዋጋ ሳይቀር ወደ መቶ ብር ደርሷል። ጨው-በርበሬ፤ ቡና-ስኳር፤ የምግብ ዘይት- ሽንኩርት- ማብሰያ እንጨት- ከሰል፤ እና ሌሎቹም ለህይወት በጣም አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች ሁሉ የኅልም እንጀራ ሆነዋል። ለድሃው ብቻ ሳይሆን፤ መካከለኛ ገቢ ላላቸው ቤተ ሰቦች ሳይቀር፤ ስጋ መብላት ተረት ሆኗል ። በዚህ ምክንያት፡-- - ዛሬ፤ ሁሉም ቤተሰብ፤ " አምላክ ማረን ማረን፤

ዶሮ መቶ አወጣ እኛም ስጋ አማረን " እያለ ይጸልያል ።

መ. ሕዝቡ በነገድና በቋንቋ እንዲከፋፈል እየተገደደ ነው ።

ሰ. ሀገሪቱ የባህር በሯ ተዝግቶባታል ። ዳር- ድንበሯ ተደፍሯል። የዓለም አቀፍ ወሰኗም ደብዛው ጠፍቷል ። ሰፊ መሬቷም ለባዕድ ሀገር ተሰጥቷል ።

ረ. የኢትዮጵያ ሀገራዊ ሀብት፤ ለም- የርሻ መሬቶች፤ ማዕደናት፤ በባዕዳን እንዲመዘበሩ ተደርገዋል ።

ሠ. ሀገርን ሊጠቅም የሚችለው የኢትዮጵያ ምሁር በሚያስደነግጥ ፍጥነት፤ ወደ ወጭ በመሰደድ ላይ ነው ። አፍለኛ፤ ትኩስና የወጣት ኃይል ጉልበት፤ ሀገሩን መጥቀም ሳይችል በመቅረቱ ወደ የፊናው እየተሰደደ ይገኛል። ስደቱ- ዘጽዐቱ፤ ሁሉንም የሀገሪቱ ኅብረተሰብ ያካትታል ። ሀገሪቱ ሰው- አልባ መሆኗ ደግሞ ወያኔን እየጠቀመው ነው።

ሸ. ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎ፤ እንዲያው ከነ አካቴው፤ የሀገሪቱ ኅልውና በአደጋ ላይ መሆኑ ማንም የሚክደው አይደለም ።

እነኝህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች፤ ከአርባ ዓመታት በኋላ፤ ከሞላ -ጎደል፤ ሀገራችን እምን ደርጃ ላይ እንደወደቀች ያስረዳሉ ። ይኅንን ሁሉ በግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ ምን መደረግ አለበት ? የሚለውን ጥያቄ በጋራ መመለስ አስፈላጊ ነው ። ይህንን ማድረግ ደግሞ፤ ለመፍትሄው ፍለጋ በር ከፋች ይሆናል፤ ብለን እናምናለን ። ያ እንዲሳካ ከተፈለገ፤ የሚከተሉትን ግንዛቤዎች በዕይታ ውስጥ ማስገባት፤ የጋራ ተግባር ለማከናወን ጠቃሚነት ይኖረዋል ብለን እንገምታለን ።

1ኛ. የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግሮች ለማስወገድ ፤ ልክ እንደ 66ቱ የካቲት ስር-ነቀል ለውጥ አስፈላጊ ነው ።

2ኛ. ይህንን ለውጥ ለማምጣት፤ የኀይል አሰላለፉን አውቆ፤ ፈርጀና አስተካክሎ መገኘት ወሳኝነት ይኖረዋል ። የኃይል አሰላለፍ ማለት፤ ወያኔንና ጸረ አንድነት ክፍሎችን በአንድ ወገን፤ በሌላ ወገን ደግሞ ያንድነት ኃይሉ ሰልፍ ማለት ይሆናል። ሌላ ሦስተኛ-አራተኛ የሚባል ነገር፤ ድሪቶ መደረት ነው። ለሁሉም ነገር የቅድሚያ-ቅድሚያ የሚሆነው የሀገራችን መኖር -አለመኖር በመሆኑ፤የኃይል አሰላለፉም የዚህ አስተጋብዖ ይሆናል ።

3ኛ. ወጣቱን ኃይል በትግል ማሰለፍ፤ ማስተማርና ማዘጋጀት በአንክሮ ሊታይ ይገባዋል። የኢትዮጵያ ሴቶች ኃይልና ሰልፍ ወሳኝ ሚና ይጫወታል ።

4ኛ. የየካቲት 66 ዓም ሕዝባዊ አመፅ የኢትዮጵያ አንጡራ ዐብዮት ኢትዮጵያዊ/ ወጥ ( ኦርጂናል ) ነበር የተባለው፤ ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጎች ያካተተ ሆኖ፤ በጎሳ፤ በሃይማኖት፤ በቋንቋና፤ በጎጥ፤ ሳይከፋፈል

ሁሉም በአንድ ላይ ቆሞ በመተባበር የነበረውን ሥርዓት በማስወገዱ ነበር ። ይህ ክስተት ሁለት መሰረታዊ የታሪክ ምዕራፎችን አስመዝግቧል ።

አንደኛው፤ ምናልባትም ከአድዋው ጦርነት ወዲህ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን አንደገና በማስረገጥ፤ የጋራ ጠላት የሆነውን ጨቋኝ ሥርዓት በጋራ ማስወገዱ ነው።

ሁለተኛው ፤ የጋራ ችግሩን ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብሮ መፍታት የሚችል ሕዝብ መሆኑን በድጋሚ ያረጋገጠበት ወቅት መሆኑ ነው። ዛሬም እንደ ትላንቱ፤ በጋራ ተባብሮ፤ ይህን ዘረኛ ሥርዓት ማስወገዱ አይቀሬ ነው ። የጋራ ጠላት ሲባል፤ የውጭ ባዕድ ወራሪን በቻ ሳይሆን፤ አገር-በቀል ጨቋኝ አገዛዝንም ያጠቃልላል።

5ኛ. የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ነገ የሚያመጣው ለውጥ፤ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ግዛታዊ ምልዑነት( ትርቶሪያል ኢንተግሪቲ ) ፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት፤ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነት፤ የሕዝቧን ዕኩልነትና መብት የሚያስገኝ፤ የሚያረጋግጥና የሚያስጠብቅ ይሆናል ።

6ኛ. ኢትዮጵያን በድርድርና በአማራጭ አስቀምጦ " ለ እኔ ያለሆነች ሀገር ብጥስጥሷ ይውጣ " የሚባልበት ዘመን ማክተሙን አምኖ መቀበል ግዴታ ነው ። ይልቁምን፤ የጋራ የሆነችውን ሀገር ሁሉም ዜጋ በጋራ ጠቃሚ ልትሆን የምትችልበትን ሥርዓት መመሥረት ዘላቂ ሠላምና ቋሚ ብልፅግና የሚያረጋግጥ መሆኑን አምኖ መቀበል ወሳኝ ነው ።

7ኛ. የሾላው ዛፍ ፍሬ ጠቃሚነቱ ለአዕዋፍ መሆኑ ባይካድም፤ የኢትዮጵያን ሀብት ሊጠቅምባት የሚችለው፤ የሞተላት እንጅ የገደላት ሊሆን አይችልም ። ለዘለዓለማዊት ኢትዮጵያ፤ ህያው ሆና እንድትኖር፤ ህይወታቸውን የለገሏት ሰማዕታት ለዘለዓለም ህያው ናቸው።

ኢትዮጵያም ለዘለዓለም ትኖራለች !!!